የቤተ አብርሃም ሰንበት ት/ቤት	2012 ዓ.ም

የጥምቀተ መዝሙሮች መድብል

ማውጫ

1. የስላሴን መንበር 1
2. ዝም አትበሉ 2
3. ቸሩ ሆይ 3
4. ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን 4
5. ገና እንዘምራለን 5
6. ዘምር ዘምር አለኝ 6
7. ንሴብሆ 7
8. አንደበቴም ያውጣ 8
9. ስምህ በሁሉ 9
10. አማን በአማን 10
11. ደስ ይበለን 11
12. አድርገህልኛል እና በቸርነት 12
13. ሰው ሆይ ደስ ይበለን 13
14. ቤተክርስቲያን 14
15. እሰይ ተወለደ 14
16. ተወለደ ጌታ ተወለደ 15
17. በኤፍራታ ምድር 16
18. በጎል በጎል 17
19. እልል እልል 18
20. ድንግል ፈጣሪዋን ወለችው 19
21. ዮሐንስኒ 20
22. የአለምን በደል 21
23. እሰይ እሰይ 22
24. የሰላሙ መሪ 23
25. የፍቅር እናት የሰላም 24
26. ማርያም እንወድሻለን 25
27. በጎ መዐዛ 26

28. ትህትናሽ ግሩም ነው 27
29. ለማርያም 28
30. ይኩነኒ 29
31. ታማልደናለች 30
32. ውዳሴ ማርያም 31
33. በምን በምን እንመስላት 32
34. ለምኚ ድንግል ለምኚ 33
35. ንዒ ንዒ ማርያም ንዒ ንዒ 34
36. የስሙ ትርጓሜ 35
37. ኃያል ኃያል 36
38. ኦ ሚካኤል 37
39. አማላጅ ነው 38
40. ገብርኤል ሃያል 39
41. የራማው ልዑል 40
42. ኦ ፍጡነ ረድኤት 41
43. ገድሉ ተአምራቱ 42
44. ብዙ ልጆች አሉት 43
45. አንች አንች ቤተልሔም 44
46. ሰላም ለኪ እያለ 45
47. ድንግል በድንግልና 46
48. መላእክቱ 47
49. አበረታኝ ፍቅርህ 48
50. ገብርኤል በሰማይ 49
51. የምስራች ዜና 50
52. ከሊባኖስ 51
53. የእቲሳ አንበሳ 52
54. ቅዱስ ሚካኤል 53
55. ሐረገ ወይን 54

56. ኦ ክርስቶስ 55
57. ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ 57
58. አምላክ ሰው ሆነ 58
59. ንዓ ንዓ ሚካኤል ንዓ 59
60. አማኑኤል አምላክ 61
61. እቴ ሙሽራዬ 62
62. የጽድቅ በር ነሽ 63
63. ሃሌ ሃሌ ሉያ 64
64. እም ድንግል 65
65. ሀይሌ ብርታቴ 66
66. ናና አማኑኤል 67
67. ባሕራንኒ ይቤ 68
68. አማኑኤል ናና 69
69. ናና ሚካኤል ናና 70
70. አንቲ ዘበአማን 71
71. ይቤላ መልአክ 72
72. ገብርኤል መልአክ 73
73. እልል በሉ 74
74. ድንቅ አድርጎልኛል 75

1. የስላሴን መንበር

የ ስላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሀል ሚካኤልን ከፊት
አእላፍ መላዕክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የ ሰማዩን አባት
እዩት ተመልክቱት የ ሰማዩን ድምቀት

የስላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የ ሰማይ መላዕክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ/3/ ሲሉ
ይህን ልዩ ክብር ሊያዩ የ ታደሉ
በፅድቅ ስራቸው ደምቀው ይታሉ
በፅድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ

የ ቅዱሳን ህብረት በቅዱሳን ሀገ ር
ሲያወድስ ይኖራል የ ስላሴን መንበር
ፅድቅና ርህራሄ የ ተመላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሳኤ እንድናይ/2/

2. ዝም አትበሉ

ዝም አትበሉ ዝም አትበሉ
እግዚአብሔርን አመስግኑ/2/
ቅዱስ/5/ በሉ መላዕክትን ሁኑ ምስጋና ጀምሩ
ቅዱስ ቅዱስ በሉ

የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን አንሺው
በምስጋና መዝሙር እግዚአብሔርን ጥሪው
አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ
ከእኛ ጋር ይሆናል የሰራዊት ጌታ/2/

ፍጥረታትም ጩሁ ሰማያት ዘምሩ
ስለቅድስናው ሁላችሁ ዘምሩ
ዳዊት ሆይ ተነ ሳ ስለ ፅዮን ዘምር
ከበሮው ይመታ በገናው ይደርደር/2/

ወገ ኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር
ውለታው ብዙ ነው ለእኛ ያለው ክብር
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ
ለጌታ ለእግዚብሔር ለሰራዊት ጌታ/2/

ባህሩን አቋርጦ ለሚያሻግራችሁ
ተራራውን ንዶ ለአቀለለላችሁ
በአውሎ ነ ፋስ መሀል መንገ ድ አለው ጌታ
ለንጉስ ክርስቶስ እንዘምር በእልልታ /2/

3. ቸሩ ሆይ

ቸሩ ሆይ ቸሩ ሆይ ናና
ቸሩ ሆይ አማኑኤል ናና
የእስራኤል መና ቸሩ ሆይ ናና
ቸሩ ሆይ መድኃኔዓለም ናና

ቸሩ ሆይ ለዓይነ ስውር መሪ
- ›› ምርኩዝ መመኪያ ነህ
- ›› አንተን የሚመስል
- ›› ምንም ነገር የለም
- ›› ምህረትና ፍቅርህ
- ›› ወሰን ወደር የለው
- ›› ሳንወድህ ወደኸን
- ›› ፈልገህ ጠራኸን

ቸሩ ሆይ ሰምተህ እንዳልሰማህ
- ›› አይተህ እንዳላየህ
- ›› ሁሉን ታልፈዋለህ
- ›› ፍቅራዊ አባት ነህ
- ›› አማኑኤል ጌታ
- ›› ቸሩ ፈጣሪያችን
- ›› ውለታህ ብዙ ነው
- ›› ለኛ የዋልክልን

ቸሩ ሆይ በከብቶች ማደሪያ
- ›› በዚያች ትንሽ ግርግም
- ›› ተወልዶ አዳነን
- ›› ጌታ መድኃኔዓለም
- ›› እልል በሉ ሰዎች
- ›› በአንድ ላይ ዘምሩ
- ›› ስብሃት ለእግዚአብሔር
- ›› በአርያም በሉ

4. ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን/2/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገ ረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን

የሰማዩን መንግስት ርስቱን ለሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን
ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል

ከአለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የ በዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስግነ ው ከጧት እስከ ማታ

በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባህር ወጀብ በሞላበት
ለእርሱ መንገ ድ አለው ከቶ ምን ተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት

በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሃና የኢያቄም የ እምነታቸው ፍሬ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስዕለቱ የሀና እምነት
ለምኚልን ለእኛ ኪዳነ ምህረት

5. ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን/4/
እንደ መላዕክቱ ብርሃንን ለብሰን
ገና እንዘምራን
ወላዲተ አምላክን ከፊት አስቀድመን
በዳዊት በገ ና መሰንቆ ታጅበን
ለስላሴ ክብር ገና እንዘምራለን
ገና እንዘምራለን
በምስጋና ስራ ከሰለጠኑት ጋር
ልብን የ ሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን
ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና
ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና
ገና እንዘምራለን
በትዕቢት ሳይሆን በታላቅ ትህትና
በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና
ስራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና
ገና እንዘምራለን
ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም
ሜልኮል በዝማሬው ብትስቅበትም
አምላክ ከወደደ እንዲያመሰግነ ው
በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ማን ነው
ገና እንዘምራለን

6. ዘምር ዘምር አለኝ

ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ
የ አምላኬን ቸርነ ት እንዴት ብዬ ልርሳ
ያደረገ ልኝን እንዴት ብዬ ልርሳ
የሚቃጠለው ስብ በፊትህ ምንድነ ው
ሰማይና ምድር ሁሉ ገንዘብህ ነው
ያለኝን ሰብስቤ ባኖረው ከፊትህ
ዋጋ አይሆንም ጌታ ስለቸርነ ትህ
ይበዛል ይሰፋል የ እግዚብሔር ምስጋና
አይቆምም በዘመን ማዕበል ነ ውና
እንኪን ድንጋይ ቀርቶ ጋራው ቢናድብኝ
የከንፈሬን ፍሬ ማንም አይወስድብኝ
የጳውሎስ የ ሲላስ መከራው ቢፀና
አልተውም ቅኔውን የ አምላኬን ምስጋና
ሊያስጥለኝ አይችልም እስር ሰንሰለቴ
አለብኝ ውለታ የ ሰማዩ አባቴ
የተደረገ ለት ብዙ የ ተቀበለ
ይኖራል በፍቅሩ እየ ተቃጠለ
ክብሬን ሁሉ ትቼ ልዘምርልህ
ይህ ነው ችሎታዬ ለአንተ የምሰጥህ

7. ንሴብሆ

ንሴብሆ/2/ለእግዚአብሔር
ስቡሀ ዘተሰብሀ/2/
ባህሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ
በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ
ከባርነ ት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን
ሕይወት የ ሚሰጠው መና ነው
ምግባችን
እናመስግነ ው/2/እግዚአብሔርን
ምስጉን ነው የ ተመሰገ ነ /2/
አስፈሪ ነው ያልነ ው ብዙ ነ ገ ር ነ በር
ሁሉንም አልፍነ ው አምላካችን ይክበር
ጉልበታችን ቢዝል ፈተናው ቢበዛ
ሀይላችን ጌታ ነው የ አለሙ ቤዛ
ከአለት ላይ ውሀ ፈልቆልን ጠጣነ ው
ይህን ታላቅ ጌታ ኑ እናመስግነ ው
ህዝቦች ደስ ይበለን ህይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

8. አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የ ምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በአይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀኃይን ያቆመ
ዛሬም ኅብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከሃጢያት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በሃይሉ የ ዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋር

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ልዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣኦት እንድሰግድ ነ ገ ስታት ቢያውጁም
ሁሉ ሊተወኝም ሊጠላኝም ዓለም
ፅናት ይሆነ ኛል ጌታ መድሃኔዓለም

9. ስምህ በሁሉ

ስምህ በሁሉ ተመሰገ ነ
ከክብርህ በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማወደስ ያስደስተናል
ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል
አምላክ ተመስገ ን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከህፃ ናት አፍ ምስጋና ይውጣ
አንተን ማመስገ ን ይሁን የ እኛ ዕጣ
በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማህሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም/2/
ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣም
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነ ትህን እንጠብቃለን
ከአንተ ደጅ ጌታ የት እንሄዳለን

10. አማን በአማን

አማን በአማን/2/
አማኑኤል ተመስገን
ለዚህ ፍቅርህ ምን እንበል
ድብቁን ሃጢያት አንተ ብትገልፀው
ይቅር ብልኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ
ለእኔ ሃጢያትስ የ ለውም ቦታ
በየደቂቃው ሐጢያት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንትን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣ በትር አልገረፍከኝም
ምህረትን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በሐጢያት መኖሬ
ዓለም በኃጢያት እየ ሳበችኝ
በፅድቅ በደስታ መኖር አቃተኝ
የሐጢያት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍፁም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

11. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን /2/ አምላክ አለ መሃላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምህረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህቺን ዕድሜ ለጨመረልን
ለንስሀ ጊዜ የ ሰጠን
ኃጢያትህን ይታገስሃል
በምህረት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የ ጽድቅ ህይወት
እልል በሉ የ ጎበኛችሁ
በምህረት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትፀልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በፅኑ ፍቅር አንድ ቢያደርገ

12. አድርገህልኛል እና በቸርነት

አድርገ ህልኛል እና በቸርነ ትህ
አመሰግንሃለው እልል እልል
ለዓለም ዓለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድሃኔዓለም

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅኸልኝ የ ልቤን ትካዜ

አምላኬ ጉልበቴ ታይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የ እምነ ት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄለሁ
ካለኝ ነ ገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ

ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የ ምመልስልህ ባላገ ኝ ስጦታ
በቀንም በሌትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባህሪህ እጹብ ለአንተ ሥራ

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል አይጎ ድል እንደገ ና

13. ሰው ሆይ ደስ ይበለን

ሰው ሆይ ደስ ይበለን በአምላካችን
ከሀጢአት ባርነ ት ነጻ ላወጣን
ተነ ሡ እናመስግን ውለታው ብዙ ነው
ምን ይከፈለዋል ተመስገ ን ብቻ ነው

በሀጢአት በሽታ ወድቄ ሳለሁኝ
መድሃኒት ክርስቶስ ከውድቀት አነሳኝ
ስጦታህ ብዙ ነው ለእኔ የ ሰጠኸኝ
ተመስገ ን ብቻ ነው አምላክ ላንተ ያለኝ

እንደ በርጠሎሚዎስ እውር የነበርኩኝ
ዛሬ ግን በአምላኬ ድህነ ት አገኘሁኝ
ህጉ ለመንገዴ ብርሃን ሆኖኛል
የእርሱ ስለሆንኩኝ ሰላሙን ሰጥቶኛል

በድንቅ አጠራርህ ለጽድቅ የ ጠራኸኝ
ከአጋንንት እስራት ነጻ ያወጣኸኝ
አልፋን ኦሜጋ ዘላለም የ ምትኖር
ኤልሻዳይ የሆንከው አማኑኤል ተመስገን

የእዳ ደብዳቤዬን ጌታዬ ቀደደው
የማዳንህን ሥራ በአይኔ አይቻለሁ
ችርነ ቱ አያልቅም ድንቅ የሆነ ው ጌታ
ስሙን እናወድስ እንዘምር በእልልታ

14. ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን ባህረ ጥበባት/2/
አትመረምርም/2/ እጅግ ጥልቅ ናት/2/
በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ
የ እምነ ት መነ ፅሩን ይዞ ስላልመጣ
አንዳንዱበስህተት/2/ ፈጣሪውን አጣ/2/
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
አንዳንዱ ቢክደው/2/ እየ ተታለለ/2/
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የ አምላክ እናት ናት
ሀበ ጥባበት ሀበ ልሳናት/2/
የ ሐንስ/2/ ወንጌለ ስብከት
የመስቀሉ ቃል ለእኛ የ እግዚአብሔር ሀይል ነው
ለማያምኑት ሞኝነ ት ነው ለእኛ ግን ህይወት

15. እሰይ ተወለደ

እሰይ ተወለደ የ ዓለም መድሃኒት/3/
ይኸው ተወለደ የ ዓለም መድሃኒት/3/
ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ ሁሉ/3/
አምላክ ቀዳማዊ ይመጣል እያሉ/3/
ሰብአ ሰገ ል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ/3/
የእስራኤል ንጉስ ወዴት ነው እያሉ/3/
ሰብአ ሰገ ል መጡ እጅ መንሻ ይዘው/3/
ወርቅ እጣን ከርቤውን ገበሩለት ሰግደው/3/
ህፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት/3/
ውሃው ሆኗልና ማርና ወተት/3/

16. ተወለደ ጌታ ተወለደ

ተወለደ ጌታ ተወለደ
ተወለደ አምላክ ተወለደ
ትንሽ ብላቴን 15 ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላዕክት አዋጅ
በፍጹም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የ ሚያድን የ ሰዎች አለኝታ
ይህ ዓለም በቃሉ ከተወለደበት
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነ በት
እንደምን ይገርማል ይኼ ተዋህዶ
አየነው አምላክን እንደ ሰው ተወልዶ
ፍጹም ድንግልና ክብርን የ ተሞላች
እንደምን አምላክን በማህጸን ያዘች
ዓለምን በቃሉ የ ፈጠረ ጌታ
ወለደችው ድንግል የ ሔዋን አለኝታ
አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም
በምድር ተፈልጎ እንደ አንቺ አልተገ ኘም
በሃሳብ በግብር ንፅህት ስለሆነ ች
ለአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

17. በኤፍራታ ምድር

በኤፍራታ ምድር በቤተልሔም/2/
ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም/2/
ብርሃናዊው ኮከብ ከሠማይ ዝቅ አለ/2/
ፍጥረትም ዘመረ ሀሌ ሉያ እያለ/2/

መንጋውን በሌሊት ሲጠብቁ እረኞች
ከሠማይም ሠሙ ታላቅ የ ምስራች
በመላዕክቱ ግርማ ምድር ስታበራ
የሚያስጨንቅ ነ በር እጅግ የ ሚያስፈራ

ድንገ ትም የ ሠማይ ሠራዊት ተገልፀው
በአንድነ ት ዘመሩ ከኖሎት ጋር ሆነ ው
ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ብለው
ሠላምም በምድር በጎ ፈቃድ ለሠው

ቤተልሔም ሄደው ጌታን ተሳለሙት
ከእናቱ ጋር ሆኖ በግርግም አገኙት
የመላዕክትን ዜና እረኞች አወሩ
በልዩ ምሥጋና አምላክን ሲያከብሩ

ለህዝቡ ሁሉ የ ሚሆን ፍስሃ ደስታ
በዳዊት ከተማ ተወለደ ጌታ
ህፃን ከእናቱ ጋር በግርግም ፈልጉት
እርሱ ነው ለሠዎች የ ድህነ ት ምልክት

18. በጎል በጎል

በጎል በጎል ሰብዓ ሰገል/2/
በጎል ሰብዓ ሰገ ል ሰገዱለት
ፀሐይ/2/ ፀሀይ ሰረቀ/2/
ፀሐይ ሰረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ/2/
አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ/2/
የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶብሽ
የ ዓለም መድሃኒት ተጠመቀብሽ
ድንግል ማርያም ንፅህይት ቅድስት/2/
የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ አንቺን መርጦሻል
እልል/2/ ደስ ይበለን/2/
ወልድ ተወልዶ ነፃ አወጣን
ዮሐንስ አጥምቆ ድልን አገ ኘን

19. እልል እልል

እልል እልል ደስ ይበለን
ወልድ ተወልዶ ነፃ አወጣን
ሰማይ ተከፍቶ ምስጢር አየን
የጥል መጋረጃ የ ተጋረደው
ከደመናት በላይ የ ተሰወረው
ግድግዳው ፈረሰ ድብቁ ተፈታ
ከድንግል ሲወለድ የ ሠራዊት ጌታ
በሥጋና በደም ሁሉን ተካፈለ
ፀና ዝምድናችን እኛንም መሰለ
በድንግል ማህጸን ሆነ ተዋህዶ
ተስፋው ተፈጸመ ክርስቶስ ተወልዶ
የ ናፈቅነ ው መሲህ ሲገለፅ ማስያስ
ህልማችን ሲፈታ ገነት ስትመለስ
ሰውና መላዕክት በአንድነ ት ዘመሩ
አስታርቆናልና ተዋርዶ ከክብሩ

20. ድንግል ፈጣሪዋን ወለችው

ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው
በመጠቅለያም ጠቀለለችው
የለምና ስፍራ ለእንግዶች ማረፊያ
ግርግም አስተኛችው በከብቶች ማደሪያ
ጨነቃት ጠበባት የ ዳዊት ከተማ
የጌታ መወለድ ተአምሩ ሲሰማ
ወረደ መልአኩ ምስራች ሊያወራ
የህፃኑ ክብር በምድር አበራ
ይህ ምስጢር ግሩም ነው ከቶ የ ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነ በር
ሰብአ ሰግል መጡ ከሩቅ ምስራቅ አገር
ወርቅ እጣን ከርቤውን ለእርሱ ለመገበር
በእናቱም እቅፍ አገኙት ህፃኑን
ለአለም ተናገሩ ንጉስ መወለዱን
ይህ ምስጢር ግሩም ነው ከቶ የ ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር
የይሁዳ ምድር ምስጋና ተመላ
ንጉስ መጥቷልና ከናዝሬት ገሊላ
ተአምሩን ትናገር ቤተልሄም ታውራ
ዝማሬ ሲውጣት ተረስቶ ቆጠራ
ይህ ምስጢር ግሩም ነው ከቶ የማይ ገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር
የ ማይታይ ታየ ተዳሰሰ እንደ ሰው
በጠባቡ ደረት ዓለሙን መሰለው
ገረማት ጥበቡ ታናሷ ሙሽራ
ተዋህዷልና ቃል ከስጋ ጋራ
ይህ ምስጢር ግሩም ነው ከቶ የማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነ በር

21. ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ያጠምቅ/2/ በሔኖን/5/
በማዕዶተ ዮርዳኖስ

ዮሐንስ ሲያስተምር ….ያጠምቅ
በጫካ በሜዳ…… ያጠምቅ
ግምል ፀጉር ለብሶ ……..ያጠምቅ
ሆኖ ምድረበዳ ……ያጠምቅ
በሔኖን/4/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ

አምላኩን የ ሚወድ …… ያጠምቅ
ብዙ ሰው እያለ……ያጠምቅ
ጌታውን ለማጥመቅ……. ያጠምቅ
ዮሐንስ ታደለ ……ያጠምቅ
በሔኖን/4/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ

ከሃጢያት ተለዩ…… ያጠምቅ
በውሃ ተጠመቁ…… ያጠምቅ
መንግስተ ሰማያት.. ያጠምቅ
እንዳለች እወቁ ……..ያጠምቅ

22. የአለምን በደል

የአለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመመስረት በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
የሰማዮች ሰማይ የ ማይችለው ንጉስ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ
ባህር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገ ረው ዳዊት በትንቢቱ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሠማያዊው አባት
እየ መሰከረ የ ልጁን ጌትነት
ባህር ስትጨነ ቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየ ች ይህን ምስጢር
እንደምናነ በው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በዕርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ

23. እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ ተጠመቀ
እሰይ እሰይ ተወለደ
ከሰማያት ሰማይ ወረደ
ከድንግል ማርያም ተወለደ
በቅዱስ ዮሃንስ ተጠመቀ
እርሱ ባይወለድ //
ቸሩ አባታችን //
እርሱ ባይጠመቅ //
ቸር አባታችን //
መች ትገ ኝ ነ በር //
ገ ነ ት ርስታችን //
እንደጠል ወረደ //
ከሰማይ ወደኛ ››
ወገ ኖቹን ሊያድን ››
ከክፉ ቁራኛ ››
ብርሃን ወጣላቸው ››
ለእምነ ት ወገ ኖቹ ››
በጨለማው ጉዞ ››
እንዲያ ሲሰለቹ ››
እግዚአብሔር አብ ላከ ››
አንድያ ልጁን ››
እርሱም ወደ ልናን ››
እንዲሁ ዓለሙን

24. የሰላሙ መሪ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ/2/
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ/2/

ወለደን በጥምቀት በመንፈስ ዳግመኛ/2/
የንጉሶች ንጉስ የፃድቃን እረኛ/2/

ለመልካሙ ሥራ በእምነት እንበርታ/2/
ከሰይጣን ባርነት ነጻ አወጣን ጌታ/2/

የዛሬው ጥምቀቱ ተነግሮ በአዋጅ/2/
ነጻነት አገኘን በእግዚአብሔር አብ ልጅ/2/

እግዚአብሔር አብ ላከ አንድያ ልጁን/2/
እርሱ ወዷልና እንዲሁ ዓለሙን/2/

25. የፍቅር እናት የሰላም

የፍቅር እናት የሠላም/2/
ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ማርያም
በህይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ
አንቺ አለሽና አጠገ ቤ
ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገዴ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ
ጠላት ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ
ትላንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ
የለም ለነገ የ ሚያስፈራኝ
ሜዳ ይሆናል ተራራ
ልጅሽ ስላለ ከእኔ ጋራ

26. ማርያም እንወድሻለን

ማርያም እንወድሻለን/2/
ስለወለድሽ የህይወት ምግብን
ማርያም እንወድሻለን

ድክመቴን አትይ ማርያም
በሃጢያት መውደቄን //
ተስፋዬ አንቺ ነሽ //
እስከ ዕለተ ሞቴ //
ላልከዳሽ ምያለሁ //
ከስርሽ ላልጠፋ //
ገፀ በረከቴ //
የህይወቴ ዋስትና //

የምዕመናን ውበት ማርያም
ዘውድ አክሊላቸው //
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ //
መንገ ድ ስንቃቸው //
ምስክር ነኝ ለአንቺ //
እንደ ነ ብያቱ //
ስጦታ መሆንሽን //
ለአዳም ልጆች ሁሉ //

ሞገስና ጸጋ ማራያም
በጌታ ፊት ያለሽ //
ከሰይጣን መሸሻ //
ዋስ ጠበቃችን ነሽ //
እንዴት ነ በር ያኔ //
ጌታን ስትወልጂው //
የ እረኞቹ ደስታ //
የ መላዕክት ዝማሬ //

27. በጎ መዐዛ

በጎ መዐዛ ሽቶዬ ነሽ
በሰዉ ሁሉ ፊት ዘመርኩልሽ
በአንቺ ጣፈጠ አልጫነ ቴ
እጠራሻለሁ ነይ እመቤቴ

ምሳሌም የ ለሽ ነይ እመቤቴ **ዘመዴ ነሽ** ነይ እመቤቴ
ያን ክፉ ዘመን ነይ እመቤቴ **ያለፍኩብሽ** ነይ እመቤቴ
በፍቅርሽ እሳት ነይ እመቤቴ **ልቤ ነደደ** ነይ እመቤቴ
እናትነ ትሽን ነይ እመቤቴ **ስለወደደ** ነይ እመቤቴ
የሰዉስ ጉልበት ነይ እመቤቴ **ምን ይረባኛል** ነይ እመቤቴ
ሰረገላዬስ ነይ እመቤቴ **መች ያድነ ኛል** ነይ እመቤቴ
ከተሰወረ ነይ እመቤቴ **ክፉ መከራ** ነይ እመቤቴ
እድናለሁኝ ነይ እመቤቴ **አንቺን ስጠራ** ነይ እመቤቴ
ለስንፍናዬ ነይ እመቤቴ **መቼ ልክ አለዉ** ነይ እመቤቴ
ስለበደሌ ነይ እመቤቴ **እተክዛለሁ** ነይ እመቤቴ
ለአነጋገ ሬ ነይ እመቤቴ **ማጣፈጫ ነሽ** ነይ እመቤቴ
ተሰምቻለሁ ነይ እመቤቴ **ድንግል ሆይ ስልሽ** ነይ እመቤቴ
የመንገ ዴ ስንቅ ነይ እመቤቴ **የ ርሀቤ መርሻ** ነይ እመቤቴ
ለታመመ ሰዉ ነይ እመቤቴ **ነሽ መፈወሻ** ነይ እመቤቴ
የተማፀነ ነይ እመቤቴ **በስምሽ አምኖ** ነይ እመቤቴ
ማን አፍሮ ያዉቃል ነይ እመቤቴ **ፊትሽ ለምኖ** ነይ እመቤቴ

28. ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም/2/
እናቱ ሆነ ሻል ለመድኃኔዓለም/2/
ንፅህት ስለሆንሽ እመቤቴ
እንከን የ ሌለብሽ //
የ ፍጥረታት ጌታ //
በአንቺ አደረብሽ //
የ ድንግል መመረጥ //
ዜናው አስገረመን //
እሳቱን ታቀፈች //
የ ማይቻለውን //
ምርኩዜ ልበልሽ እመቤቴ
ጥላ ከለላዬ //
ጋሻዬ አንቺ ነሽ //
ለእኔ መመኪያዬ //
በዓለም እንዳልጠፋ //
ሕይወቴ መርሮብኝ //
እንደ ወይን አጣፍጪው //
ማሪያም ድረሽኝ //
የ ምስራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ
የ ሁላችን ደስታ //
እሙ ለፀሃይ ፅድቅ //
የ ሁሉ ጠበቃ //
ድንግል የ ድል አክሊል //
ድንግል የ ፅድቅ ሥራ //
ድንግል መሰላል ነሽ //
የ ተዋህዶ ተስፋ //

29. ለማርያም

ለማሪያም/2/
እንዘምራለን ለዘላለም/2/
የ ተዘጋች ደጅ ለዘላለም
ህዝቅኤል ብሏል //
ንፅህት ናት በእውነ ት //
በፍፁም ድንግል //
አብነ ት አድርግን //
እኛም እርሱን //
በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን/2/
የ ዋሂት ርግብ ለዘላለም
ሰላም አብሳሪ //
የ ጨለመ ህይወቴን //
ብርሃንን አብሪ //
እምጸንሻለሁ //
ድንግል ለነፍሴ //
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ/2/
እጅግ የ በዛ ነው ለዘላለም
ያለኝ ፍቅር //
አይነገርም //
አይወሰንም //
በእርሷ ደስ ይለኛል //
ሃሴት አደርጋለው //
ስሟን እየ ጠራሁ እዘምራለሁ/2/
ንዒ ንዒ ስላት ለዘላለም
ቀንና ሌሊት //
አትለየ ኝም //
ለእኔስ ቅርቤ ናት //
እፁብ እፁብ ብለው //
አመሰገ ኗት //
ክብሯን ሊገ ልፁ ቢያጥራቸው ቃላት/2/

30. ይኩነኒ

ይኩነ ኒ በከመ ትቤለኒ/2/
አለች የ እኛ እናት በትህትና
በስጋ በነ ፍስም ንፅህት ናትና
አለች የ እኛ እናት በትህትና
ድንግል በክሊዬ ንፅህይት ናትና
የአዳም ቃል ኪዳን መፈፀሚያው ሲደርስ
ላከው ገብርኤልን ወደ ቤተ መቅደስ
በእግዚአብሔር ህሊና ተስላ የነበረች
ከሰማይ የመጣ ቃሉን ተቀበለች
ዳግሚት ሰማይ አርያም ሆነ ች
ይደረግ ብላ በትህትና ተቀበለች
ማርያም ሆይ አትፍሪ ብሎ እያረጋጋት
ከአንቺ የ ሚወለደው መድሃኒት ነው አላት
ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል
ብላ ጠየ ቀችው ድንግልም ደንቋታል
ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ
በህግ ሳይሆን በድንግልና ትወልጃለሽ
ህይወት ሊቀዳባት አድሯል በማህፀንዋ
አይኖርም ከእንግዲህ የ ሄዋን መርገ ሚ
ለአዲሱ ኪዳን አዲስ ብስራታችን
ምክንያተ ድህነ ት አለች እናታችን
ቃልህ ይፈፀም ይደረግ ብላ
ታምር ተሰማ ኢየ ሩሳሌም ናዝሬት ገ ሊላ
እጅግ አስገረመን የ ገብርኤል ዜና
የእነ ዘካሪያስ ከቶ አይደለምና
ለተመረጠችው የደረሰው ብስራት
አለምን ከመሞት ከመርገ ሚ ዋጃት
ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ
በህግ ሳይሆን በድንግልና ትፀንሻለሽ

31. ታማልደናለች

ታማልደናለች ታማልደናለች/2/
ማርያም/2/ ቤዛዊት ዓለም/2/
ሚካኤል መልአክ ሊቀ መላእክት/2/
ዘአውረድከ/2/መና ከደመና/2/
ገብርኤል መልአክ አብሰራ ትስብእት/2/
ዘአብሰራ/2/ ለማርያም ንፅህት/2/
ሩፋኤል መልአክ ሊቀ መላዕክት
ዘአብርሃ/2/ዓይኖ ለጦቢት/2/
ዑራኤል መልአክ ለዕዝራ ነብይ/2/
ዘአስተዮ/2/ ፅዋዕ ልቦና/2/
ሰሎሞን ይቤላ/4/
ዕርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ/2/
ገብረ መንፈስ ቅዱስ/2/
ሐዋርያ/2/ ዘእስክንድርያ/2/
ተክለ ሐይማኖት/4/
ሐዋርያ/2/ ዘኢትዮጵያ/2/
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ
አዕማደ/2/ ቤተክርስቲያ/2/

32. ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮሃለሁ ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ ወድሰኒ ልጂ በይኝ
ውዳሴ ማርያም በሰርክ ፀሎት ላይ
// ዜማ ስናደርስ
// ድንግል ትመጣለች
// ከቤተ መቅደስ
// የ ብርሃን ምንጣፍ
// ከፊቷ ተነ ጥፏል
// ቅዱስ ኤፍሬም
// ታጥቶ የ መሰግናታል
ውዳሴ ማርያም አባ ሀርያቆስ
// ምስጋና ያደርሳል
// የቅዳሴው ዜማ
// ልብን ይመስጣል
// በጎ ነገር ልቤ
// አወጣሁ እያለ
// ዳዊት በገናውን
// እየ ደረደረ
ውዳሴ ማርያም የንፅህናችን
// መሰረት ነ ሽና
// አንቺን ለማመስገ ን
// ልቡናዬ ይብራ
// ተፈስሂ ድንግል
// ኦ ቤተልሄም
// ካንቺ ተወለደ
// መድሃኔዓለም
ውዳሴ ማርያም ቅዱሳኑ ሁሉ
// ዙሪያሽ ከበዋል
// አባ ጊዮርጊስም
// ንዒ ድንግል ይላል
// በወርቅ ዙፋን ላይ
// ተቀምጠሽ ሳይሽ
// ልቤ ተሰወረ
// ድንግል በግርማሽ

33. በምን በምን እንመስላት

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን/2/
ምሳሌ የ ላትም የ ላትም ከብሯን የ ሚመጥን/2/
የሙሴ ፅላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ
የመላዕክት እህት የሩህሩሃን ርግብ/2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዲዮን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት ያፃድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማህደር/2/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግስት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ/2/
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነ ው በልጅሽ ነ ው ና
እናታችን ፅዮን ይድረስሽ ምስጋና/2/

34. ለምኚ ድንግል ለምኚ

ለምኚ ድንግል ለምኚ/2/
ለኃጥአን/3/ አይደለም ለፃድቃን
ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ
›› አዛኝ ሩህሩህ ነሽ
›› የ ጌታዬ እናት
›› ፀጋን የ ተሞላሽ
›› የ አምላክ ማደሪያ
›› ለምነሽ አስምሪኝ
›› አማናዊት ፅዮን
›› ከእኔ አትለይኝ
ለምኝ ሐዘንሽ ሐዘኔ
›› ለእኔ ይሁን ድንግል
›› የተንከራተትሽው
›› በሃገረ እስራኤል
›› ትዕግስትሽን ሳየ ው
›› ልቤ ይመሰጣል
›› የሀዘን እንባ ጎርፍ
›› ኣይኔን ይሞላዋል
ለምኝ በቀራንዮ አንባ
›› በዚያ የ ፍቅር ቦታ
›› በዕግረ መስቀሉ ሥር
›› ከክርስቶስ ጌታ
›› ለእኛ ተሰጥተሻል
›› እናት እንድትሆኚን
›› ልጆችሽ ነንና
›› ምልጃሽ አይለየ ን
ለምኝ አንደበቴን ጌታ
›› በምስጋና ሙላው
›› ደስ ይበልሽ ብዬ
›› እኔም ላመስግናት
›› አንደበቴን ጌታ
›› በምስጋና ሙላው
›› ደስ ይበልሽ ብዬ
›› እኔም ላመስግናት

35. ንዒ ንዒ ማርያም ንዒ ንዒ

ንዒ ንዒ ማርያም ንዒ ንዒ
ድንግል ሆይ ንዒ ንዒ
ያን የአሳት ባህር ከቶ እንዳላይ

በሐመረ ኖህ የተመሰልሽ
በአሮን በትር የተመሰልሽ
<u>የምሥራቋ በር</u>/2/ ቶሎ ድረሽ

በተራራማው በኤፍሬም ሀገር
እንግዳ የሆንሽ ለኤልሳቤጥ በክብር
<u>ነይልኝ ወደ እኔ</u>/2/ ከአንቺ ጋር ልኑር

ዓለም ከብዶብኝ ተጨንቄአለሁ
ሐዘን በዝቶብኝ ብቸኛ ሆኜአለሁ
<u>እረ ነይ ድንግል ሆይ</u>/2/ እጠራሻለሁ

ጥበቡ አንቺ ነሽ ለሰሎንዲስ
ነይ ብሎ የሚጠራሽ ሶላናጢስ
<u>አትጥፊ ድንግል ሆይ</u>/2/በእጅስ ልዳሰስ

ምሥጢር የገለጽሽ ለሕርያቆስ
ፈጥነሽ ያማለድሽ በቤተ ዶኪማስ
<u>ነይልኝ እናቴ</u>/2/ ልቤ ይፈወስ

ድንግል ቀርባለች ጩኸቴን ሰምታ
የኃጢአቴ ገመድ እስሩ ተፈታ
<u>አከብራታለሁ</u>/2/ ልጇ በእልልታ

36. የስሙ ትርጓሜ

የሥሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው
የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው
እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው
ከጉድጓድ ተጥሎ ፍዑም ከሚያስፈራው
ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው
እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን
ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን
የክፉ ሰው ሥራው ክፉ ሃሳብ ነ ውና
በቅንነ ት መንገ ድ ከቶ አይሄድም እና
የሞቱን ደብዳቤ ለባህራን ሲሰጠው
ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው
ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ
ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምስጋናን ጀምሬ
ጸጋዬን አብዝቶ ላበቃኝ ለዚህ ክብር
የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

37. ኃያል ኃያል

ኃያል ኃያል /2/ ሰዳዴ ሳጥናኤል/2/
ኃያል ገባሬ ኃይል
ባህራንን ያዳነ ው
ተላፊኖስን የ ረዳው
መልአኩ ሚካኤል ነው/2/
የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው
ከእደ ረበናት/2/ሶስናን የዳናት/2/
ሚካኤል መልአከ ምህረት
ዲያብሎስን ያዋረድከው
በእሳት ሠይፍ የቀጣኽው
ሚዛንህ ትክክል ነው/2/
ሚካኤል ክብርህ ድንቅ ነው
በሀዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና/2/
አፅናናኝ አረጋጋኝ/2/
ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

38. አ ሚካኤል

አ ሚካኤል/2/ ሊቀ መላዕክት
በኃጢያት እንዳንወድቅ እንዳንሞት
ፈጥነ ህ ተራዳን አፅናን በእምነ ት
ለያዕቆብ ወገ ን ሚካኤል
ለእስራኤል //
ጠባቂያቸው ነህ //
መልአከ ኃይል //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚካኤል የእኛ አባት/2/
ነጸብራቃዊ //
ተክህኖ ልብስ //
ሀመልማለ ወርቅ //
ዓይኑ ዘርግብ //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚካኤል የ እኛ አባት/2/
በስዕልህ ፊት //
እስግዳለሁ //
ቀርበህ አነ ጋግረኝ //
አለሁ በለኝ //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚካኤል የ እኛ አባት/2/

39. አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳዩ መልአክ ጠባቂ የእስራኤል
የመላዕክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል
አማላጅ ነው ሚካኤል/2/
የአምላክ ባለሟል
ለእነ ሙሴ ለህዝበ እስራኤል
ፈርኦን በእስራኤል ላይ በትዕቢት
ተነ ስቶ ቢከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
ከባህር ያወጣኸው ጸጋዘአብን
ከአረመኔው ንጉስ እግዚአርአን
ከልልህ የጠበክ በብዙ ተአምራት
እኛንም ጠብቀን ከበደል ከኃጢያት
በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነ ህ የደረስከው ሊቀ መላዕክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ፈጥነ ህ ድረስልን ሁነን እረዳት
መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሀለን እንድትብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነ ን ሚካኤል አደራ

40. ገብርኤል ሃያል

ገብርኤል ሀያል መልአከ ሰላም መልአከ ብስራት
የምታወጣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከሚነ ድ እሳት
ፍቅርህ ተስፏል ከልባችን
ፊትህ ቆመናል ባርከን ብለን
የፅናታቸው ዝናው ሲሰማ
ከዛች ባቢሎን ከሞት ከተማ
ህፃናት ሳሉ በራ እምነ ታቸው
ቆመህ ተገኘህ መሃካላቸው
ውሃው ሲዘንም ቢያስደነ ግጠን
በጋኖቹ ውስጥ ቢነ ዋወጥም
ጸንተው ዘመሩ ልጅና እናቱ
አንተ ስላለህ ከዚያ ከሳቱ
ቂርቆስም ፀና ሞትን ሳይፈራ
አንተ ስላለህ ከእነ ርሱ ጋራ
አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ
አምነ ው ድል ነሱ ያንን መከራ
እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ
ቆመኽ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ
ክፉውን ዘመን የማልፍበት
ፅናትን ስጠኝ ድል ልንሳበት

41. የራማው ልዑል

የ ራማው ልዑል ገ ብርኤል/2/
ተመላለስ መሃላችን ስምህን ጠርተን ንዓ ስንል
የምስራች ነጋሪ ድንቅ ልደት አብሳሪ
የፅድቅ የፋና የህይወት ጎዳና/2/
የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል ጠባቂያችው
ከእሳት ነበልባል ያዳንካቸው/2/
ተስፋችን ነህ መመኪያችን
ቅዱስ ገ ብርኤል አባታችን/2/
ላመኑብህ ለተማጸኑህ
ፈጥኖ ደራሽ አለኝታቸው ነህ/2/
እሳት ለብሰህ ብርሃናዊ መልአክ
አንተ አማልደን ከመሃሪው አምላክ/2/

42. አ ፍጡነ ረድኤት

አ ፍጡነ ረድኤት/2/
የ እግዚአብሔር አገ ልጋይ ቅዱስ ሰማዕት
ሠላም ለአንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የ ልዳው ጸሀይ ››
በጨካኝ ንጉስ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገ ልጋይ ነህ ››
ሥቃይ ያልበገ ረህ ››
አክሊልን አገ ኘህ መከራን ታግሰህ
የ ፈጣሪውን ስም ››
ስለመሰከረ ››
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሠይፍ ተመተረ
የ ስቃይ መሣሪያ ››
ያላዘናጋህ ››
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ
ለእምነ ት ተጋዳይ ››
ታማኝ ወታደር ››
ቢነ ገ ር አያልቅም የ ተሰጠህ ክብር
ሥቃይ ቢያደርሱብህ ››
በመታገ ስህ ››
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ
ለሠማው ይደንቃል ››
የ አንተ ሰማዕትነ ት ››
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉ ፍጥረት
ገድልህ ይነ ገ ራል ››
ክብር እንደተሰጠህ ››
ጊዜ የ ማይሽረው ምግባር ሀይማኖት ነው

43. ገድሉ ተአምራቱ

ገድሉ ታምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣኦትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋህዶ ኮከብ ተክለሃዋርያ
አባ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
ዳግማዊ ዮሃንስ ጠፍር የታጠቀ
ንፁህ ባህታዊ ጠላት ያስጨነ ቀ
የፀጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ
ደካማ መስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት
ባለ 6 ክንፉ ተክልዬ የ እኔ አባት
እርሱ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አስቦ
ሌጊዮን ሲዋረድ እፍረት ተከናንቦ
ከካህናት መካከል ህሩይ ነው ተክልዬ
መጣሁ ከገ ዳምህ ልሳለምህ ብዬ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት
የባረከው ውሃ የረገጥከው መሬት
ገላህ ያረፈበት ሆኗል ፀበል እምነ ት
ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

44. ብዙ ልጆች አሉት

ብዙ ልጆች አሉት ለስሙ ምስክር
በዙሪያው ያሉትን አብቅቷል ለክብር
ስለፍጹም ምልጃ ለኔ ግን ይለያል
መላኩ ሚካኤል ስለው ደስ ይለኛል
ከመላእክት ክብሩ ከፍ ከፍ ብሎ
በአምላክ ተሸመው ዘንዶውንም ጥሎ
አሳዳጊዬ ነው ሆኖ እናት አባቴ
ሚካኤል ባለበት ይሸሻል ጠላቴ
ከሚታየው ሁሉ ልቤ ከሚፈራው
ካላየሁት ነገር ጠላት ከሰወረው
ያድነኛል ፈጥኖ በመንገዴ ወጥቶ
ሚካኤል ሀያሉ ክንፎቹን ዘርግቶ
በባህራን ታሪክ በነተላፊኖስ
በአፎምያ መትረፍ በነ ዱራታአስ
በነብዩ ዳንኤል መች ፈጸምና
የሚካኤል ስራ ቀጥላል ገና
በጉዞ የረዳችሁ በባህር በየብሱ
ፈጥኖ ደርሶላችሁ እንባን ስታፈሱ
ስለታችሁ ሰምሯል ቁሙ በዝማሬ
በሚካኤል ምልጃ የቆማችሁ ዛሬ
ክብር ለሚገባው ክብር እንሰጣለን
ንጉስ ለወደደው እንሰግድለታለን
እንኪን ለሚካኤን ለሚቆም ጌታ ፊት
ክብር እንሰጥ የለ ለምድር ሹማምንት

45. አንች አንች ቤተልሔም

አንች አንች ቤተልሔም የይሁዳ መሬት (2)
ባንች ተወለደ የዓለም መድኃኒት (2)
ለአዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ››
ጌታ ተወለደ ››
ከድልግል ማርያም ››
እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም
የምስራቅ ነገስታት ››
ሕጻኑን ከእናቱ ››
ተኝቶ ላገኙት ››
እሰራኤልን በግብጽ ቤተልሔም
የሚጠብቃቸው ››
ከአንች ይወጣል ብሎ ››
እንደነገራቸው ››
ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም
ያሸበሸቡብሽ ››
ስብሐት ለእግዚአብሔር ››
ብለው ዘመሩብሽ ››
አንች ቤተልሔም ቤተልሔም
እንዴት ታድለሻል ››
ኢዮርና ራማ ››
ኤረርን መስለሻል ››

46. ሰላም ለኪ እያለ

ሰላመ ለኪ እያለ (2)
ሐርና ወርቁን ስትስማማ
የገብርኤል ድምጽ ተሰማ
ተሰማ የመልአኩ ድምጽ ተሰማ
ተሰማ የገብርኤል ድምጽ ተሰማ

ውኃ ስትቀጅ ክንፉን እያማታ
ሊያበስርሽ የመጣው በታላቅ ደስታ
ከሞገስሽ ብዛት (2) ሲታተቅ ሲፈታ
አቅርቦልሽ ነበር የክብር ሰላምታ

የምስራቹን ቃል ምስጢር ተሸክሞ
ገብርኤል ተላከ ሊያረጋጋት ደግሞ
እርጋታን ተሞልታ (2) ነገሩን መርምራ
የመልአኩን ብስራት ሰማችው በተራ

ይደሰታል እንጅ መንፈሴ በአምላኬ
በምስጋና ሳድር ዘወትር ተንበርክኬ
ሐሳቤ ለቅጽበት (2) ሌላ መች ስባል
ለኔ ልጅን መውለድ እንዴት ይቻለኛል

ካንች የሚወለደው ንዑድ ነው ክቡር
የተመሰገነ በሰማይ በምድር
ምስጢሩ ኃያል ነው (2) ይረቃል ይሰፋል
ካንች በቀር ይህን ማን ይሸከመዋል

እፁብ ነው ድንቅ ነው አንቺን ፈጠረ
አንችን በመውደዱ ሰውን አከበረ
ዓለምን ይባረካል (2) በማህጸንሽ ፍሬ
ክብርሽን አልዘልቀው ዘርዝሬ ዘርዝሬ

47. ድንግል በድንግልና

ድንግል በድንግልና ፀንሳ
በድንግልና ትወልዳለች
ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች
ገና ሳይፀነስ ዘመኑ ሳይገባ
ገረድ መሆን ሻተች ትንቢቱን አንብባ
ልታያት ናፈቀች ያችን ቅድስት እናት
ለክብሯ ተገዝታ ውሃ ልትቀዳላት
ባሪያ ልሁን አለች ዝቅ አድርጋ ራሷን
መች አወቀችና እናቱ መሆኗን
ጥቂት ለሚሻ ሰው ያውቃል ብዙ መስጠት
በማህፀኗ መቅደስ ሲቀደስ ኖረበት
ሐር ወርቁን ስትፈትል በቤተ መቅደሱ
ማደሪው እንድትሆን መረጣት ንጉሱ
በህሊናው ተስላ የነበች ምናብ
መሰላል ሆነችው ለአዳም ድህነት ርካብ
በጎ መአዛዋን ውበቷን ወደደ
በማህፀኗ ሊያድር እግዚአብሔር ወረደ
ከኪሩቤል ይልቅ ጀርባዋ ተመቸው
ንጽህት ናትና የማትቆረቁረው
የተዘጋች መቅደስ ከቶ ማትከፈት
ታትማ ኖረች ክብሩ ሰገነት
ማንም አይከፍታትም ጥበብ አላትና
የእስራኤል ቅዱስ ገብቶባታልና
በረቀቀው ጥበብ ድንግል ተደነቀች
በሆዷ ቅዳሴን እያስተናገደች
ጎንበስ አለች ማርያም ውዳሴ ልትሰማ
ከቅንያት አለም ከሆዷ ከተማ

48. መላእክቱ

መላእክቱ በፊቱ ይቆማሉ
ሰራዊቱ በፊቱ ይሰግዳሉ
ኃያል አምላክ እግዚአብሔር እያሉ (2)
በክብረ መንግስቱ በነጭ ዙፋን ላይ
ዘለኣለም ይኖራል ከሰማያት በላይ
ለሚታዘዙለት እጁን ይዘረጋል
ጨለማውን በሰላም ያነጋል
መብረቅ ነጎድጓዱ የምስጋናው ጅረት
ዘወትር ይፋሰል በቀንና ሌሊት
የእሳት መጋረጃው ይነዳል ከፊቱ
ተቀኙለት ሊቀ መላእክቱ
ትናንትናም ዛሬም እርሱ ያው እርሱ ነው
ሞትን አሸንፎ በአባቱ ቀኝ ያለው
ዳግመኛ ሲመጣ እርሱን ለመቀበል
በደመና እንነጠቃለን
በወርቅ ፅና ላይ ብዙ ዕጣን ጨምረው
ዙፋኑን ያጥናሉ በበጉ ፊት ቆመው
አዲሱን ምስጋና አዲሱን ውዳሴ
ያቀርባሉ ለቅድስት ሥላሴ

49. አበረታኝ ፍቅርህ

አበረታኝ ፍቅርህ ጌታዬ
አበረታኝ ክንድህ አምላኬ
በስምህ ድኛለሁ በፀጋህ
በማደሪያህ ሆኜ ስጠራህ
ሰዶም ስትቃጠል መርገሟ ሲበዛ
ሊተወኝ አይሻም ልጁን እነደዋዛ
ህጉን በማክበሬ አምላክ ፈረደልኝ
ጎትቶ ሚያዎጣ መልአክ ሰደደልኝ
በገናን መደርደር አያቆምም ጣቴ
የወንጭፌ ድንጋይ አንተነህ ጉልበቴ
የሳኦልን ካባ አውልቀህ ጣልክልኝ
የፍልስጤሙን ሰው ክንድህ ሰበረልኝ
ሶስት ጊዜ ስክድህ አላውቅህም ብዬ
ዶሮ ስለጮኽ ትዝ አልከኝ ጌታዬ
ወጣሁኝ በዕንባ ከአይሁድ እሳት ስር
ከሐዲ ሳትለኝ አኖርከኝ በፍቅር
ሳምራዊት ናት ሳትል ክብርን የሰጠኸኝ
እንደ አንተ ከአይሁድ ፍቅር ማን አሳየኝ
ምስጢሬን በሙሉ ነገርከኝ ጌታዬ
የፍቅር ውሃ ቀዳሁ እንስራዬን ጥዬ

50. ገብርኤል በሰማይ

ገብርኤል በሰማይ ኤልሳቤጥ በምድር (2)
ይመሰክራሉ ድንግል ያንችን ክብር (2)
ትፀንሲ ሲልሽ በከበረ ዜና
ይሁንልኝ አልሽው ትውልድ እንዲፅናና
ከገብርኤል ሰምተው መላእክቱ ሁሉ
ለበጉ ማደሪያ ክብርን ይሰጣሉ
ብፅዕት እንላለን እኛም አደግድገን
የራማውን ልዑል አብነት አድርገን
ስርሽ በምድር ነው ሃረግሽ በሰማይ
ነፁህ መሶበ ወርቅ የተመላሽ ሲሳይ
የማህፀንሽ ፍሬን በላነው ጠጣነው
በኤፍራታ ሰምተን በዱር አግኝተነው
የተሰወረውን መና በልተነዋል
ከተመረጡት ጋር ብፅዕት ብለናል
ከተፈጥሮ በላይ ጽንስን ያዘለለ
የእሳት ምሰሶ ባንች ተተከለ
የእግዚአብሔር ሃገሩ የእንጀራ ቤታችን
ምንኛ ድንቅ ነው ክብርሽ እናታችን
ብፅዕት እንላለን እኛም አደግድገን
ቅድስት ኤልሳቤጥን አብነት አድርገን
ተወልዶ በግርግም ተኝቶ ስላዩት
ሰውና መላእክት አብረው አከበሩት
የጥሉ ግድግዳ በልጅሽ ፈረሰ
በዳግማዊት ሔዋን የአዳም ዘር ተካሰ
እጅ እንነሳለን ሆነን በትህትና
ክብርሽን መመስከር ክብራችን ነውና

51. የምስራች ዜና

የምስራች ዜና በገብርኤል ታወጀ
ሰላምና ፍቅር በዓለም ላይ ደረጀ
የመላእክትና የእረኖች ዝማሬ
ቤተልሔም ባንች ተፈጸመ ዛሬ
የምስራች ደስ ይበለን በልደቱ ሊቀድሰን
መድኃኔአለም ሊባርከን አማኑኤል ሊባርከን
የነቢያት ትንቢት ደረሰ የድንግልን ሥጋ ለበሰ
ሐዘን ጠፋ ሰላም ነገሠ (2)

የነቢያት ትንቢት ሲደርስ ሰዓቱ
ጌታ ተወለደ ከድንግል እናቱ
ለፍቱራን ሁሉ የሚሰጥ መኖሪያ
ተኝቶ ተገኘ በእንስሳት ማደሪያ

ቤተልሔም ባንች ግሩም ቃል ተሰማ
መላእክት እና የእረኞች ዜማ
በቅዱስ ልደቱ እኛን ሊያድነን
ወረደ ከሰማይ ተወለደልን

የጌታዬ እናት ድንግል ንጽሕይት
ክብር ይገባሻል ምንግዜም በእውነት
ጌታን የታቀፉ ንጹሐን እጆችሽ
በረከት ያድሉን ለኛ ለልጆችሽ

52. ከሊባኖስ

ከሊባኖስ (2) ከልጅሽ ጋር ነይ
እመ አዶናይ ከሊባኖስ ወደ እኛ ነይ

ጥበቃሽ ዘወትር ከሊባኖስ
እንዳይለየኝ ››
በሄድኩበት ሁሉ ››
ማረፊያ ሁኚ ››

እኔ ባሪያሽን ከሊባኖስ
ድንግል አትርሽኝ ››
በጽድቅ ሰሌዳ ››
ስሜን ጻፊልኝ ››

ነፍስና ስጋዬን ከሊባኖስ
አደራ እልሻለሁ ››
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ››
ተማጽኜሻለሁ ››

ከመሞቴ በፊት ከሊባኖስ
ለንስሃ አብቂኝ ››
ለነፍሴ ማረፊያ ››
አዘጋጅልኝ ››

ከንበሶች መኖሪያ ከሊባኖስ
ከነብሮች ተራራ ››
መጥተሽ አስደስቺኝ ››
እህቴ ሙሽራ ››

የልብስሽ መአዛ ከሊባኖስ
የሊባኖስ ሽታ ››
ሮማን ናርዶስ ነሽ ››
እናቱ ለጌታ ››

እመቤቴ ስልሽ ከሊባኖስ
ስምሽን ስጠራ ››
ፈጥነሽ ድረሽልኝ ››
ከቅዱሳን ጋራ ››
ከሚካኤል ጋራ ››
ፈጥነሽ ድረሽልን ››
ከገብርኤል ጋራ ››

53. የእቲሳ አንበሳ

የእቲሳ አንበሳ ተክልዬ ተነሣ
ወገንክን ታደገው ከኃጢአት አበሳ
ተኩላው ለምድ ለብሶ በእርግጥ መጥቷልና
ጴጥሮስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና
ዮሓንስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና
ኩቃስ ዝም አትበል እንደጥንቱ ቅና
ማርቆስ ዝም አትበል እንደጥንቱ ቅና
ጳውሎስ ዝም አትበል እንደ ጥንቱ ቅና
የዓለም ምናምነቴ የተባልከው ቅዱስ
የዋሁ መነኩሴ አባ ሕርያቆስ
ቅዳሴ ማርያምን ናና ዛሬም ቀድስ
በእጣኑ መዐዛ ድውያንን ፈውስ (2)
ወንጌል አንበሣ ጎርጎርዮስ ፍጠን
ምሶሶው ሳይወድቅ መንጋው ሳየበተን
መብረቁ አትናቴዎስ ሞገዱን ገስፀው
አፈ ጉባኤያችን በመስቀልህ ዳኘው (2)
መርከቧን የሚያውክ ነፋስ መጥቷልና
አምላካችን ፈጥነህ አድነን ቶሎ ና
ጴጥሮስ ሆይ ቀስቅሰው ልንጠፋነው ብለህ
ሞገዱ እያየለ ዝም እንዳይል ጌታ (2)
ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ቶሎና
ኖላዊ እረኛ ያስፈልጋልና
ሥጋውን የጎዳ ነፍሱን የጠቀመ
ነቅ ጉድፍ የሌለው ግብሩ የታረመ (2)

54. ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚካኤል (3) ነፍሴ ሲጨነቅ ስዝል ስጋዬ
ፈጥተህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ
አንተ ስለሆንክ ሚካኤል
ያምላክ ባለሟል ››
ልመናህ ፈጥኖ ››
ካምላክ ያቀርባል ››
የዋህ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው (2)
ደዌ የጸናበት ሚካኤል
ባንተ ይድናል ››
በአደባባይህ ››
ምስክር ሆኗል ››
ከቤትህ መጥቶ የተማፀነ
በቃል ኪዳንህ ሕይወቱ ዳነ (2)
ካምላክ ተሰቶህ ሚካኤል
ክብርህ ያበራል ››
ለጎስቋላው ሰው ››
መጠጊያ ሆኗል ››
ትልቅ ትንሹ ደሃው ሐብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ካምላክ በስሙ (2)
በብሉያ ኪዳን ሚካኤል
ከአምላክ ተልከህ ››
ሕዝበ እስራኤልን ››
ነፃ ያወጣህ ››
በአድስ ኪዳንም ድንቅ ስራ አለህ
በተአምራትህ ትፈውሳለህ (2)
ባለመድኃኒት ሚካኤል
ያቃተውን ››
ፈዋሽ ፀበልህ ››
ሆኖኛል ኃይልህ ››
እንደመጻጉ ድኅነት አገኘሁ
ፈውሰኸኛል ባንተ ተመካሁ (2)

55. ሐረገ ወይን

ሐረገ ወይን (4)
እመብርሃን
የጸጋ ሁሉ ምንጭ
የሕይወቴ ተስፋ
እስኪ ላመስግንሽ
ሳላፍር በይፋ
ምርኩዜ ልበልሽ
ጥላ ከለላዬ
የእኔ መመኪያ
ዕንቁዋ ጋሻዬ ሐረገ ወይን
መልከሰሚቱ ሽቱ
የሕሙማን ፈውስ
የአብ ቃል እናቱ
ስንቅ ዕፀ ጳጦስ
መዓዛሽ ተስማሚ
የሕይወት ምግብ
የቅንነት መዝገብ
የሰላም ርግብ ሐረገ ወይን
የአቤል መሥዋዕት
የዳዊት መዝሙር
የአሪን ክህነት ነሽ
ጸአዳ ጸምር
የስደተኞች ቤት
ማረፊያ ድንኳን
የልባችን ደስታ
እመቤታችን ሐረገ ወይን
እንደ ወይን እንደዘለላ (2)
የጻድቃን እመቤት የጽድቃችን ጥላ
ስምሽ የጣፈጠ ግሩም ነው ወለላ
ማርያም ርግብየ ይቤላ

56. አ ክርስቶስ

አ ክርስቶስ አ አምላክ ብሩህ ነህ (2)
ልቦናዬን አብራው በጥዑም ቃልህ (2)
የታቦር ደመና ክርስቶስ
የሲና ልምጫ ››
ምነው ሙሴን በሆኩ ››
እንዳይ ቀድሜ ››
የዮርዳኖ ውኃ ››
በላይ ሲፈላ ››
ዮሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ
ነበልባል ሐመልማል ክርስቶስ
ተዋህዶ ሲና ››
ሙሴ ከሩቅ ሆኖ ››
ተመልክቷልና ››
በቀረበ ጊዜ ››
ነገሩን ሊረዳ ››
ለእስራኤል ሾምከው ሁሉን እንዳይጎዳ
ሙሴ በበትሩ ክርስቶስ
ኤርትራን ሲመታ ››
ተሻገሩ እስራኤል ››
በብዙ ደስታ ››
ያልተደሰቱማ ››
የፈርኦን ሰራዊት ››
እየተሳጠሙ ቀሩ ወደ ኋሊት
ትንቢቱ ጸደቀ ክርስቶስ
የኢሳይያስ ››
ድንግልም ወወለደች ››

በመንፈስ ቅዱስ ››
ምነው ባደረገኝ ››
እንደነሰሎሜ ››
ዴታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቁሜ
ሐዋርያት ሁሉ ክርስቶስ
ዞረው ያስተማሩት ››
ወንጌልህ ብርሃን ነው ››
የዓለም መድኃኒት ››
ዮሐንስ እንዳለው ››
ጥምቀት ለንስሐ ››
እታጠበዋለሁ የጎንህን ውኃ
ሚካኤል በቀኝህ ክርስቶስ
ገብርኤል በግራ ››
ቅውጣን የሆኑት ››
ሁሉም በየተራ ››
ሱራፌል ኪሩቤል ››
ዐይናቸው የበዛ ››
ያመሰግኑሃል አንተን የዓለም ቤዛ

57. ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ

ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ
ተጠለይ በእግዚአብሔር ታዛ
ከሚራራልን ፍቅር ከሁነው
ዘላቂ ሰላም ከእግዚአብሔር ነው
ይህን እወቂ ይህን ተረጅ
በልብሽ ጉልበት ለርሱ ስገጅ
በሰይፍ ያልቃሉ ሰይፍ የሚያነሱ
የሚራራልን ሲፈርድ ንጉሱ
በቀል የርሱ ነው አይደለም ያንች
በፀጋው ታጥረሽ በፀሎት በርች
የውጣ ውረድ የጉስቅልናው
በእግዚአብሄር ነው መከራ ማብቅያው
ሰላ ይሁን ሲል ይሆናል ሰላም
ያሳዬሽውን ፍቅር አይራሳም
ማራት ኢትዮጵያን ማራት ሃገሬን
በየሄድኩበት መጠሪያ ስሜን
ይባቃት ሌሊቱ ይውጣላት ፀሀይ
አሁን ይዘርጋ እጅህ ከሰማይ
እንድትፈራርስ ጠላት ሽምቋል
ብርቱውን ጉልበት ከአፈር ደባልቋል
ይህን ግፍ አስብ ዘንበል በልላት
ካንተ በስተቀር መሄጃ የላት

58. አምላክ ሰው ሆነ

አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ
በድንግል ማርያም ተከናወነ
የአብ ሙሽራ የወልድ እናቱ
የመንፈስ ቅዱስ ፅርሃ ቤቱ
በሠማይ ሆሆ አብ አጸናሽ
ወልድም ለራሱ ቤት አረገሽ
መንፈስ ቅዱስ ነው (2) ጸለለሽ
ከሦስቱ አካል ወልድ አንዱ አካል
መጣ ወረደ በገባው ቃል
ተፀንሶ ሳለ ወልድም ከናቱ
አልተነጠለም ከሦስትነቱ
ታምራት አርጓል ድውይ ፈውሷል በአምላክነቱ
ይህንን ምስጢር በሉ ግሩም
ምስጋና አቅርቡ ለዘላለም
በስነፍጥረት ይታወቃል
የአለም ፈጣሪ የእግዚአብሔር ቃል
ደስ ይበላችሁ ደስ ይበለን በሉ እልል

59. ንዓ ንዓ ሚካኤል ንዓ

ንዓ ንዓ ሚካኤል ንዓ ንዓ
ንዓ ንዓ ሚካኤል ና ወደእኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

የባህራንን ጽፈት ሚካኤል ንዓ
የሞቱን ደብዳቤ ››
ቀደህ ስትጥለው ››
ተደሰተ ልቤ ››
ሚካኤል መሪ ነህ ››
ሊቀ መላእክት ››
በኃይል ጠብቀን ››
አጽናን በእምነት ››

ንዓ ንዓ ገብርኤል ንዓ ንዓ
ንዓ ንዓ ገብርኤል ና ወደእኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

ከእሳት ውስጥ ተጥለን ገብርኤል ንዓ
ኃይሉ ከበዛበት ››
ተስፋችን ጽኑ ነው ››
ከላይ ከሰማያት ››
መጣልኝ ገብርኤል ››
ከእሳት መጋል ቁሚል ››
የነበልባሉን ኃይል ››
በመስቀል ገስጹዋል ››

ንዓ ንዓ ሩፋኤል ንዓ ንዓ
ንዓ ንዓ ሩፋኤል ና ወደአኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

ፈታሔ ማህፀን ሩፋኤል ንዓ
ለጭንቅ ደራሽ ››
ገድልህ የሚያስገርም ››

ለደቄ ፈዋሽ ሩፋኤል ንዓ
እንዳበራህለት ››
የጦቢትን ዓይን ››
የእኛንም ልቦና ››
መጥተህ አብራልን ››
ንዓ ንዓ ራጉኤል ንዓ ንዓ
ንዓ ነዓ ራጉኤል ና ወደእኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ
ብርሃናዊው መልአክ ራጉኤል ንዓ
ሥልጣንህ ግሩም ነው ››
የሀገር ጠባቂ ››
መልአከ ሰላም ››
ተስፋዬ ደብዝዞ ››
ጨለማ ሲውጠኝ ››
በረድኤት ከበህ ››
ብርሃንህን ስጠኝ ››
ንዓ ንዓ ዑራኤል ንዓ ንዓ
ንዓ ነዓ ዑራኤል ና ወደእኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ
ሰውነቴ ደክሞ ዑራኤል ንዓ
በደዌ ሲመታ ››
ነፍሴን ሲያንገላታት ››
የኃጢያት በሽታ ››
ተአምሩን በማሰብ ››
ጸናሁ ተማፅኜ ››
ዛሬ ዘምራለሁ ››
በፀበሉ ድኜ ››

60. አማኑኤል አምላክ

አማኑኤል አምላክ ምስጋና ይገባሃል
ለአዳም ልጆች ሁሉ ምህረትን ሰጥተሃል
እልልታ ይገባል ለታላቁ ጌታ
ምህረትን ለሰጠን በኃጢያታችን ፈንታ
አዝ...
እንደ ምስኪን ደሃ አንገቱን ቀልሶ እሰይ የምስራች
ምህረት ላረገልን እንባችን አብሶ ››
ከባርነት ቀንበር ፍጹም ነጻ አወጣን ››
ደስ ይለናል ባንተ በትንሳኤው ብርሃን ››
አዝ ...
ከለሜዳ ለባሶ እርቃኑን የቆመው እሰይ የምስራች
የእኛ መድኃኔዓለም ሞትን ድል አረገው ››
ጨረቃና ከዋክብት ደም ያለቀሱለት ››
ሞትን ድል ለነሳው እናመስግን በእውነት ››
አዝ ...
መግደላዊት ማርያም በጣም ደስ ይበልሽ እሰይየምስራች
አምላክሽ ተነስቷል ከኃጢያት ሊያነጻሽ ››
እናንተ ሐዋርያት በእምነት የጸናችሁ ››
ፋራቻ ይወገድ ተነስቷል ጌታችሁ ››
አዝ ...
ንገሩ ለዓለም ያረገላችሁን እሰይ የምስራች
ከሲኦል እሠራት ያላቀቃችሁን ››
እሰይ የምስራች ሰይጣን ድል ተመታ ››
ዝማሬን እናቅርብ ሁላችን በደስታ ››

61. እቴ ሙሽራዬ

እቴ ሙሽራዬ ሰላሞን ያለሽ (2)
እኔም ልበልሽ እናቴ እመአምላክ ግቢ ከቤቴ
እኔም ልበልሽ እናቴ ማርያም ግቢ በቤቴ
አዝ...
ሁሉም ሰው ለራሱ ወንበር ሲዘረጋ
የክብርን ሽልማት ለራሱ ሲያስጠጋ
ድንግል እንደባሪያ ውሃ ተሸክመሽ
ጌታን በትህትና ታገለግያለሽ
ነይ በደመና (4) እመመቤታችን ርህይተ ህሊና
አዝ...
ወርቀዘቦ ለብሰው በቤቱ ከሞሉት
በሀርና በእብቁ ከተንቆጠቆጡት
በሰው ፊት ያማሩ ብዙ ሁነው ሳለ
ጌታ ግን ወደደሽ እናቴ ነሽ አለ
ነይ በደመና (4) እመመቤታችን ርህይተ ህሊና
አዝ...
አሳድጎሽ ሳለ መላኩ መግቦ
ተሸልመሽ ሳለ በዝቶልሽ ተውቦ
እጅግ በትህትና ስላገለገልሽው
እንደ ኪሩብ መላክ ጌታን ተሸከምሽው
ነይ በደመና (4) እመመቤታችን ርህይተ ህሊና

62. የጽድቅ በር ነሽ

የጽድቅ በር ነሽ የሙሴ ጽላት
አክሊለ ሰማእታት ምእራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹህ አክሊላችን
ሐመልማለ ሲና እመቤታችን (2)

እመቤታችን ለእኛ ምርኩዝ ነሽ

- **ከለላም ሆንሽ**
- **የእሳት መዳይ**
- **እሳት ታቀፍሽ**
- **በብርሃን ነተከበሽ**
- **ወርቅ ለብሰሽ**
- **ከሴቶች ሁሉ**
- **አብ መረጠሽ**

እመቤታችን ድንግል ሆይ ልጆችሽ

- **ዘውትር ይጠሩሻል**
- **ስምሽን ለልጅ ልጅ**
- **ያሳስቡልሻል**
- **በተሰጠሽ ጸጋ**
- **በአማላጅነትሽ**
- **ምህረትን አሰጭን**
- **ከምሃሪው ልጅሽ**

እመቤታችን ያልታረሰች እርሻ

- **ዘር ያልተዘራባት**
- **የሕይወትን ፍሬ**
- **ሰጠችን የኛ እናት**
- **የታረደው መሲህ**
- **እናቱን ወደዳት**
- **በቀኙ ቁማለች**
- **ድንግል እመቤት ናት**

እመቤታችን የእውነት ደመና

›› ዝናብ የታየባት
›› ወዳናለች ድንግል
›› የታመነች ገነት
›› ክብርት ለሆነችው
›› ኑ እንዘምርላት
›› ደስ ይበልሽ እንበል
›› ለብርሃን እናት

63. ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሃሌ ሉያ (2)
በሰማይ በምድር ምህረት ሆኖዋልና
ሃሌ ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌ ሉያ

ማላእክት ዘመሩ አመሰገኑት
እየተደነቁ በአምላክ ቸርነት (2)
ስብሃት ልእግዚአብሔር በሰማያት አሉ
እረኞችም አብረው እርሱን አከበሩ (2)

ዓለምን ለመፍጠር ከተጠበበባት
ይበልጣል ከሁሉ እኛን ያዳነበት (2)
ከዳግማዊት ሔዋን ከእመቤታችን
በረቂቅ ጥበቡ ተወልዶ አዳነን (2)

ሁላችሁም ሒዱ ከቤተልሄም
ታገኝታላችሁ በከብቶች ግርግም (2)
ኢየሱስ ክርስቶስ ወሀቤ ሰላም
ሙታችንን ወስዶ ሕይወቱን ሰጠን (2)

ወልደ እግዚአብሔር መጣ ከላይ ከሰማይ
ፍቅር አወረደው ከመንበሩ ከላይ (2)
አልተጸየፈውም መሆን ከግርግም
ትህትናው ደነቀን የመድኃኔዓለም (2)

64. እም ድንግል

እም ድንግል (3)
ተወልደ አማኑኤል

ትንቢት ተናገሩ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
ነብያቱ ሁሉ ›› ›› ››
አምላክ ቀዳማዊ ›› ›› ››
ይወርዳል እያሉ ›› ›› ››
መጣ ተወለደ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
የፍጥረታት ጌታ ›› ›› ››
ድምጹን ሰማነው ›› ›› ››
ይሄው በኤፍራታ ›› ›› ››
በአጭር ቁመትና አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በጠባብ ደረት ›› ›› ››
ተወስኖ አየነው ›› ›› ››
በከብቶች በረት ›› ›› ››
ሰብአሰገል መጡ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በኮከብ ተመርተው ›› ›› ››
ዕጣን ወርቅ ከርቤ ›› ›› ››
እጅ መንሻ ይዘው ›› ›› ››
ሰላም ተወጠነ አማኑኤል ተወልደ አማኑኤል
በምድር በሰማይ ›› ›› ››
እያሉ ዘመሩ ›› ›› ››
መላእክት በሰማይ ›› ›› ››

65. ሀይሌ ብርታቴ

ሀይሌ ብርታቴ ክብሬ ሞገ ሴ/2/
የዘለዓለሙ የ አብርሀሙ ሥላሴ /2/
ተመረጠች ነ ፍሴ አንተን ለማወደስ
ከላይ ከአርያም ከሥላሴ መቅደስ
በአንድነ ት ሦስትነ ት በዙፋኑ ሞልቶ
የ ሚሳነ ው የ ለም ለሥላሴ ከቶ
ከመንገ ድዳር ልቁም የ ወደቀ ላንሳ
የ ተራበ ላብላ የ ታመመ አልርሳ
እንደ አብርሀም አርገኝ እንደ ደጉ አባት
ቤቴ እንዲሞላ ባንተ በረከት
ጠፈሩን በውሃ በጥበብ የ ሠራ
እኔ ስ ይገርመኛል የ ስላሴ ሥራ
ኑና ተመልከቱ ታምራት ሲሠራ
ሰዎች እልል በሉ ወላድ ሆነ ች ሳራ
አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ወዶናል
ወልድ በተዋህዶ እኛንም መስሎናል
ኃይሉ ተገ ለጠ የ መንፈስ ቅዱስ
በቅዱሳን አድሮ ሲያድን ሲፈውስ

66. ናና አማኑኤል

ናና አማኑኤል ናና መድኃኒቴ
እለምንሃለሁ እስከለተ ሞቴ (2)
ረዳትም የለኝ ና መድኃኒቴ
ጠባቂም የለኝ (2) ››
የሚጣቁ አማኑኤል ››
አለሁህ በለኝ ››
እግዚአብሔር አምላኩን ና መድኃኒቴ
አዳም አሳዝኖ ››
ምድረ ፋይድ ወረደ ››
እራቁቱን ሆኖ ››
ተሰዶ አልቀረም ና መድኃኒቴ
አዳም በሲኦል (2) ››
ተወልዶ አዳነው ››
ከማርያም ድንግል ››
የነብያት ትንቢት ና መድኃኒቴ
የእስራኤል መና (2) ››
ወላዲተ አምላክ ››
ነይ ነይ በደመና ››
ሰማዕታትን ለደም ና መድኃኒቴ
አነሳሳሃቸው ››
ጻድቃን በገዳም ››
አንተ አጸናሃቸው ››
እኛም እንድንጸና ››
በእምነት በምግባር ››
በኤፍሬም ውዳሴ ››
ሁኚ ከእኛ ጋር ››
እናት አግኝቻለሁ ና መድኃኒቴ
የማትሰለች (2) ››
ቢርበኝ ብበላው ››

ስሚ የሚመች ››
ቢጠማኝ ብጠጣው ››
ስሚ የሚመች ››
አንቺ ቅድስት አገር ና መድኃኒቴ
ደብረ ሊባኖስ ››
በጻድቁ ጸሎት ››
በመንፈስ ቅዱስ ››
ሕማሙን ዳኑብሽ ››
በስጋም በነፍስ ››

67. ባሕራንኒ ይቤ

ባሕራንኒ ይቤ (6)
ባሕራንኒ ይቤ እኸ ዘነገደ ባህር
ርኢክዎ ለሚካኤል ወሰዕንኩ ጠይቆቱ ዘይብል
ባሕራንኒ ይቤ (6)
የሞቱን ደብዳቤ ባሕራንኒ
ሚካኤል አጥፍቶ ››
ባሕራን አዳነው ››
በሠርግ ተክቶ ››
ሠዳዴ ሳጥናኤል ››
ሊቀ መላእክት ››
እኛንም አድነን ››
ከሲዖል እሳት ››
ከሊቀ ነብያት ባሕራንኒ
ከነሚሴ ጋራ ››
ሕዝበ እስራኤልን ››
ሚካኤል ሲመራ ››
ቀን ደመና ጥሎ ››
ሌሊት እያበራ ››
ተሸገሩ ኤርትራን ››
ሁሉም በየተራ ››

68. አማኑኤል ናና

አማኑኤል ናና መድኃኔአለም ናና አማኑኤል ናና
በቀኝህ ለመቆም እንሻለን እኛ አማኑኤል ናና

እግዚአብሔር አምላክ አማኑኤል ናና
በገሀድ ይመጣል መድኃኔዓለም ናና
የሚያቃጥል እሳት አማኑኤል ናና
በፊቱ ይነዳል መድኃኔዓለም ናና
ፍሬና ገለባን አማኑኤል ናና
በሥልጣኑ ይለያል መድኃኔዓለም ናና

ጌታ ስትመጣ አማኑኤል ናና
በሚያስፈራ ግርማ መድኃኔዓለም ናና
መላእክት ሲነጉዱ አማኑኤል ናና
ከሰማ ከራማ መድኃኔዓለም ናና
ማነው የሚቆመው አማኑኤል ናና
ከጻድቃን ከተማ መድኃኔዓለም ናና

ለአንት የሚያስደስት አማኑኤል ናና
ምግባርን ሳልሰራ መድኃኔዓለም ናና
ምን ትመልስ ይሆን አማኑኤል ናና
ነፍሴ ስትጠራ መድኃኔዓለም ናና

ኩናኔውበርትዕ ነህ አማኑኤል ናና
ፈታሄ በጽድቅ መድኃኔዓለም ናና
ባለፀጋ ደሀ አማኑኤል ናና
ብለህ የማትንቅ መድኃኔዓለም ናና
ቸርነትህ ይርዳኝ አማኑኤል ናና
ሲያል እንዳንወድቅ መድኃኔዓለም ናና

ትናፍቀኛለች አማኑኤል ናና
መንግሥተ ሰመሰያት መድኃኔዓለም ናና
ዘላለምበሙሉ አማኑኤል ናና
ሰላም ያለባት መድኃኔዓለም ናና
ከእመብርሃን ጋር አማኑኤል ናና
የምኖርባት መድኃኔዓለም ናና

69. ናና ሚካኤል ናና

ናና ሚካኤል ናና (2)
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና
ናና ሚካኤል ናና

የረዳህ አፎሚያን ሚካኤል ናና
ሰይጣን ሲፈትናት ›› ››
አንተነህ ያዳንከው ›› ››
ባሕራህን ከሞት ›› ››
ለእነርሱ እንደመጣህ ›› ››
እኔንም ተራዳኝ ›› ››

ሚካኤል ደግፈህ ሚካኤል ናና
ለመንግስቱ አብቃኝ ›› ››
አዝኛለሁና ባንተ ልጽናና
ናና ሚካኤል ናና

ናና ገብርኤል ናና (2)
አዝኛለሁና ባንተ ልጽናና
ናና ገብርኤል ናና

ዘመኑ ሲፈጸም ገብርኤል ናና
አምላክ መምጫው ሲደርስ ›› ››
ገብርኤል አንተ ነህ ›› ››
ያልካት ያበልሽ ደስ ›› ››
ድምጽህን አሰማኝ ›› ››
ነፍሴ ጽድቅን ትልበስ ›› ››
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና
ናና ገብርኤል ናና

ናና ዑራኤል ናና
አዝኛለሁና ባንተ ልጽናና
ናና ዑራኤል ናና
ቆመህ ጽዋ ይዘህ ዑራኤል ናና

ለእዝራ ሱቱኤል ›› ››
ጥበብ ሰጠጥተህ ›› ››
ዕውቀት ስታድል ›› ››
ተገለጠ ክብርህ ›› ››
መላኩ ዑራኤል ›› ››
ድኜ በጸበልህ ›› ››
በአውደ ምህረትህ ላይ ›› ››
እኔም ዘመርኩልህ ›› ››
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና
ናና ዑራኤል ናና

70. አንቲ ዘበአማን

አንቲ ዘበአማን (2)
ረከብኪ ጸጋ ግብር ድንግል (2)
የዓቢ ክብራ ለማርያም
በይ እንግዲህ ድንግል ዘበአማን
ከእኛ አትሸሽ ››
የክርስቲያኑን ልብ ››
ትጎጽናን አላብሽ ››
የያሬድ ጸናጽል ››
የዘውትር ቅዳሴ ››
የአባሕርያቆስ ››
የዘወትር ቅሳሴ ››
የምታምር ርስት ዘበአማን
ሰለሞን ያለሽ ››
ሽጋስን አንስቶ ››
ወልድም ቀደሰሽ ››

71. ይቤላ መልአክ

ይቤላ መልአክ ለማርያም (2)
ትወልዲ ወልደ ንጉስ በቤተልሔም

ይቤላ መልአክ ከጌታ ተልከ
›› ›› ቅደስ ገብርኤል
›› ›› ሰላምታ አቅርቦላት
›› ›› ለማርያም ድንግል
›› ›› ትወልጃለሽ አላት
›› ›› ቀዲሚውን ቃል

ይቤላ መልአክ ማህደረ መለኮት
›› ›› ማርያም ውድስት
›› ›› የህዝብ ሁለ እናት
›› ›› እህተ መላእክት
›› ›› እሙ ለብርሃን
›› ›› ደብተራ ፍፅምት

ይቤላ መልአክ ወገባቲ ሃኒ
›› ›› ሐመልማለ ወርቅ
›› ›› ትበርሂ እምፀሀይ
›› ›› ሆህተ ምስራቅ
›› ›› ሰላም ለኪ ድንግል
›› ›› በአልባሰ ወርቅ

ይቤላ መልአክ ወላዲተ አምላክ
›› ›› ማርያም ንፅህይት
›› ›› ወትትሌአሊ እም አድባር
›› ›› ስብህት ወብሩክት
›› ›› ኦ ምልዕተ ፀጋ
›› ›› እግዚአብሔር ምስሌኪ
›› ›› ብሩክት አንቲ እምአንስት
›› ›› ድንግል በህሊናኪ

72. ገብርኤል መልአክ

ገብርኤል መልአክ ተጨንቃለች ነፍሴ
በል ማልደህ አስታርቀኝ ከቅዴመ ስላሴ/2/

ገብርኤል መልአክ ከእሳት የሚያወጣ
›› ›› እምነት ባይኖረኝ
›› ›› የጌታ ባሪያነኝ
›› ›› ፈጥነህ አድነኝ
›› ›› ፈታኝ ብዙ ነዉ
›› ›› የነፍሴ ጠላት
›› ›› ክንፍህ ይሸፍነኝ
›› ›› በቀን በለሊት

ገብርኤል መልአክ ማን አፍሮ ይሄዳል
›› ›› አምኖ በስላሴ
›› ›› አምላኬ እግዚአብሔር ነዉ
›› ›› ዋስ ሁናት ለነፍሴ
›› ›› በጥቂት በብዙ
›› ›› ማዳን ይቻልሀል
›› ›› የተፍለቀለቀን
›› ›› ዉሃን አብርደሀል

ገብርኤል መልአክ ኢየሉጣም ትምጣ
›› ›› ማዳንህን ታውራ
›› ›› ቂርቆስም ይናገር
›› ›› ያንተን ድንቅ ስራ
›› ›› ነገስታት ተገርመዉ
›› ›› እጃቸዉን ያዙ
›› ›› ገብርኤል አንተ ነህ
›› ›› ታምራትህ ብዙ

73. እልል በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩ ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
በኃጥያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላለን ጠላቶቹ ስንሆን
ዉለታዉ ብዙነዉ ክብር ለርሱ ይሁን/2/

እራሱን አዋርዶ እኛን ካከበረን
ስጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነዉ የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰዉ ለመዴኃኔዓለም /2/

ህይወቱን የሰጠን እንደምላክ ማን አለ
ለሰዉ ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩ የማይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወረዶ ሆነ ከእኛ ጋራ/2/

ስራዉን እናድንቅ እንድህ ለወደደን
ከማያልቀዉ ፍቅሩ በረከት ያድለን
ለማይነገረዉ ለአምላክ ስጦታ
ዉዳሴ እናቅርብ እዘምር በልልታ/2/

74. ድንቅ አድርጎልኛል

ድንቅ አድርጎልኛል የሰራዊት ጌታ/2/
አልረሳኝም አምላክ አነሳኝ ከትቢያ
ዴንቅ አድርጎልኛል በደሌን ሳይቆጥር
›› ›› ወደቤቱ ጠራኝ
›› ›› እረክሼ ሳለሁ
›› ›› ልጄ ሆይ ና አለኝ
›› ›› በዳግም ምጽአቱ
›› ›› መንግስቱን ሊያወረወሰኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ከአንበሳ መንጋጋ
›› ›› ከጉድጓድ አወጣኝ
›› ›› በጠላቶቼ ፊት
›› ›› ግርማ ሞገስ ሰጠኝ
›› ›› ምን እመልሳለሁ
›› ›› እንዴህ ለወደደኝ
ድንቅ አድርጎልኛል ጠላቶቼ ሁሉ
›› ›› ሲዋደዱብኝ
›› ›› ማን ይደርስለታል
›› ›› እያሉ ሲሉኝ
›› ›› ፈጥነህ ደረስክልኝ
›› ›› ከሞት አዳንከኝ